# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

መጋቢት 16 ቀን 2004 ዓ. ም

## የአስተማሪዎችን የስራ ማቆም አድማ ኢሕአፓ ይደግፋል!

የወያኔ አገዛዝ በአስተማሪዎች ላይ ሲያደርስና ሲፈጽመው የቆየው ግፍና በደል በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ማኅበራቸውን አፍርሷል፤ መሪዎቻቸውን አስሯል፤ ገድሏል፤ ለስደት ዳርጓል፤ ከሥራ አባሯል፤ የኑሮና ሥራ ሁኔታቸውን አቃውሷል። ወያኔ ጸረ ዕውቀት ነውና ጸረ አስተማሪ መሆኑ የሚጠበቅ ነው። ይህን ሁሉ በመቃወምና መብታችውን ለማስከበር የኢትዮጵያ አስተማሪዎች የጀመሩትን የሥራ ማቆም አድማና ትግል ኢሕአፓ ሙሉ በሙሉ መደገፉን ዳግም ይገልጻል።

በጎንደርና ሌሎች ቦታዎች የጀመረው የአስተማሪዎች የሥራ ማቆም አድማ በመስፋፋት ላይ ነው። በአዲስ አበባም አስተማሪዎችና ተማሪዎች እየተንቀሳቀሱ ናቸው። ይህም መስፋፋት ያለበትና ሙሉ ድጋፍን ማግኘት ያለበት ነው። አስተማሪዎች ቀናቸው፣ ሆነላቸው ሲባል የሚያገኙት ደሞዝ በነፍስ ወከፍ ደረጃ በጣም ዝቅተኛና ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ከቶም የማይመጣጠን መሆኑ የታውቀ ነው። ዛሬ ኪሎ ቅቤ ከሁለት መቶ ብር በላይ እያወጣ ባለበት ለአስተማሪዎች ተደረገ የተባለው የደሞዝ ጭማሪ 142 (አንድ መቶ አርባ ሁለት) ብር ነው። ለዚህም ነው የአስተማሪዎች ፍትሓዊ ትግል ሙሉ ድጋፍን ማግኘት የሚገባው። የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች፣ ተማሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ የቢሮ ሰራተኞች፣ የአየር መንገድና የመብራት ኃይል ሠራተኞች፤ የውሀ ክፍል ሠራተኞች እንዲሁም ባጠቃላይ በየፋብሪካው የሚሠሩ ሠራተኞችና ታክሲ፣ ኣውቶቡስ ነጂዎች፤ ሼኮችና ቄሶች፣ ...ወዘተ ሁሉም አስተማሪዎች በጀመሩት አድማ ተባባሪና ተካፋይ በመሆን የካቲት 66ን እንዲደግሙ ኢሕአፓ ጥሪውን ያስተላልፋል። ከአረመኔው ወያኔ መገላገያ ጊዜው ደርሷልና አይለፈን አያምልጠን ይላል ኢሕአፓ። ወያኔ የአስተማሪዎችን ትግል ለማፈን የጀመረውንና እያካሄደ ያለውንም አፈና ኢሕአፓ ያውግዛል ።

ለዴሞክራሲ በኢትዮጵያ በተደረጉ ትግሎች አስተማሪዎችና አንጋፋው ማኅበራቸው ኢመማ ብዙ መስዋዕትነትን ከፍለዋል። ዛሬም እየከፈሉ ናቸውና ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ሊተባበራችውና ከጎናቸው ሊቆም ግዴታ አለበት። ከተባበርን ከዚህ በፊት ከህዷዎች ያከሸፉትን የሙት ከተማ አድማ በመላ የኢትዮጵያ ከተሞች ማድረግም እንችላለን።

ከታጋይ አስተማሪዎች ጎን እንቁም!
የሥራ ማቆም አድማው ይስፋፋ!
ሕዝብ አቸናፊ ነው!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com